# ‹‹አነጋጋሪው የአቶ ስዬ ንግግር››

*መስፍን ወልደ ማርያም*
ጥር 2002

ጥር 26/2002 በተጠቀሰው ርእስ በአቶ የማነ ናግሽ የተጻፈውን አነበብሁት፤ መነሻውና ዋናው ጉዳይ አቶ ስዬ 1. ‹‹እኔ በተምቤን ካላሸነፍሁ፣ ገብሩ በመቀሌ ካላሸነፈ ምርጫው ተጭበርብሯል ማለት ነው፤›› ብሎ በቴሌቪዥን ሲናገር መስማቱ ነው፤ አንድ በሉ። ቀጥሎም አቶ ስዬ ሲያብራራ 2. ‹‹ኢሕአዴግ በምንም ተአምር እኔን የሚያሸንፍ ተወዳዳሪ ሊያመጣ እንደማይችል አውቃለሁ፤›› አለ፤ ሁለት በሉ። አቶ ስዬ የተናገረው ‹‹እውነት›› ነው ብሎ በማመኑ 3. ‹‹እውነት መናገር አያስቀጣም፤›› አለ፤ ሦስት በሉ። ይበቃናል።

ከላይ የተጠቀሱትን የአቶ ስዬ አባባሎች በሪፖርተር ላይ የጻፈው ሰውም ሆነ ከሰበሰባቸው የሌሎች ሰዎች አስተያየቶች ጋር ስናመሳክር በአገራችን በጣም ተስፋፍቶ የሚታየውን የአስተሳሰብ መዛባትና ፈር መልቀቅ በገሀድ የሚያሳይ ነው፤ የቀረቡት ትችቶች ሁሉ የባሕርይን ወይም የፖሊቲካ ብልጠትን የሚያመለክቱ ናቸው።

እስቲ ሦስቱን አነጋገሮች ለየብቻ እንያቸው፤ የመጀመሪያው አነጋገር **አስተሳሰቡ** የምርጫን ብቻ ሳይሆን የማናቸውንም ዓይነት ውድድር ዓላማንና መንፈስን የሚያፈርስ ነው፤ የአስተሳሰብ ስሕተቱ ያለው ስዬና ገብሩ ማሸነፋቸውን እንደማይጠራጠር መግለጹ ላይ አይደለም፤ ይህ የሱ ተስፋና እምነት ነው፤ ማንም ተወዳዳሪ እሸነፋለሁ ብሎ አይጀምርም፤ የማሸነፍ እምነትን ይዞ መነሣት አለበት፤ ግዙፍ የአስተሳሰብ ስሕተት የሚመጣው ስዬና ገብሩ ‹‹**ካላሸነፉ ምርጫው ተጭበርብሯል**›› ማለቱ ላይ ነው፤ ይህ አነጋገር ከተስፋና ከእምነት የዘለለና **መጪውን በእርግጠኛነት ሙሉ በሙሉ በብቸኛነት የመቆጣጠር** ችሎታ ወይም ኃይል እንዳለው ማስመሰል ነው፤ ቦቅሰኛው መሀመድ አሊም ቢሆን ‹‹አሸንፋለሁ›› ብሎ ይፎክራል እንጂ ‹‹ካላሸነፍሁ›› ብሎ ቦቅስ አይጋጠምም ነበር። አቶ ስዬ ውድድር ምን ማለት እንደሆነ አለመገንዘቡን የሚያሳየው ውጤቱን በቅድሚያ ማረጋገጡ ብቻ ሳይሆን እሱ እንደሚፈልገው ካልሆነ የውድድሩን ዳኝነትም **በቅድሚያ** አለመቀበሉ ነው።

ሁለተኛው አነጋገሩ ላይ ያለው የአስተሳሰብ መዛባት ‹‹በምንም ተአምር እኔን የሚያሸንፍ ተወዳዳሪ›› በወያኔ ውስጥ የለም ማለቱ ነው፤ ራሱን ሰባተኛው ሰማይ ላይ ማውጣት መብቱ ነው፤ ሌሎችን አንጦርጦስ ለመክተት ግን መብት የለውም፤ ስለወያኔ ያለውን የተወሰነ እውቀት መጠራጠር አይቻልም፤ ነገር ግን አቶ ስዬ ስለወያኔ ያለው እውቀት በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በተለይም በአለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ብዙ ሊለወጥ መቻሉን አልተገነዘበም፤ ወይም አልተቀበለም፤ ወያኔ ሁሉ በአቶ ስዬ አእምሮ ውስጥ ተጠርንፎ አልተያዘም፤ ዱሮም ሆነ አሁን እኔን የመሰለ ሰው በወያኔ ውስጥ ‹‹በምንም ተአምር አይገኝም›› ማለት ከእውቀትም ከእምነትም የዘለለና የአስተሳሰብ መዛባትን የሚያመለክት ነው።

ሦስተኛው አነጋገሩ የአስተሳሰቡን መዛባት በገሀድ የሚያወጣው ነው፤ አቶ ስዬ ከላይ የተዘረዘሩት አባባሎች ‹‹እውነት›› ናቸው ብሎ ያምናል፤ ስለዚህም ‹‹እውነት መናገር አያስቀጣም፤›› ይላል፤ እውነት ምንድን ነው? የነገን እውነት የሚያውቅ ሰው አለ? አቶ ስዬ የነገውን እውነት አውቃለሁ ነው የሚለው፤ ትንቢት እውነት የሚባለው ከተፈጸመ በኋላ ነው እንጂ በትንቢትነቱ እውነት ሊሆን አይችልም፤ እውነት የሆነ፣ የተደረገ፣ የተረጋገጠና የተመሰከረለት ነገር ነው።

የአቶ ስዬ የተዛባ አስተሳሰብ የዛሬን ከነገው፣ እውቀትን ከእምነት፣ እውነትን ከትንቢት የማይለይ በመሆኑ ግራ ያጋባል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የሰጡት

አስተያየትም እንደዚሁ የተዛባና የግል ፍላጎታቸውን የሚያንጸባርቅ እንጂ ከአቶ ስዬ የአስተሳሰብ ስሕተት ጋር እምብዛም አይገናኝም፤ እኔን የሚያሳስበኝና የሚያሳዝነኝም የአንዱን ሰው የአስተሳሰብ ስሕተት ይዞ ለመወንጀል ወይም ስሕተቱን ወደጥፋት ለመለወጥ መሞከር እየተለመደ መሆኑ ነው፤ አንዳንዴም በዚሁ ስለአቶ ስዬ በተጻፈው ላይ አንዳንድ ሰዎች ከስሕተቱ ተነሥተው ወደውዳሴ ሲያመሩ ሰውዬው በስሐተቱ እንዲገፋበት ይረዱታል።

ከአቶ ስዬ የአስተሳሰብ መዘባት ይበልጥ ለአገሪቱና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም የሚያሰጋ የሚመስለኝ እንደአቶ ሴኩ ቱሬ ያለው ምኑንም ከምኑ መለየት የማይችል የአእምሮና የመንፈስ ሚዛን፤ ቀዩንም፣ ነጩንም፣ ሰማያዊውንም ጥቁር እየቀባ የማይታየውን እንደሚያይ፣ የማይሰማውን እንደሚሰማ፣ የማይንቀሳቀሰውን እንደሚንቀሳቀስ አስመስሎ የጥላቻና የጠብ መልእክትን የሚያስተላልፍ የአስተሳሰብ መዛባት በትምህርት በመገራት ሊቃና ይችላል፤ የመንፈስ መበላሸት ግን በትምህርት አይፀዳም፤ እኔ በእንደዚህ ያለ የጎደፈ መንፈስ ልለው የማልችለውን ነገር ብሏል ተብዬ፣ ተከስሼ ተፈርዶብኛል፤ አሳፋሪ ነው፤ በቀጥታ የተባለውን ነገር መተቸት ችሎታው የሌለው ሰው ድንበር አቋርጦ ኤርትራ ይገባል!